# የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ

# Ethiopian Border Affairs Committee

P. O. Box 9536 Columbus, Ohio 43209 USA E-mail: ethiopianborders@gmail.com

# "ውሸት ቢደጋገም እውነት አይሆንም"

## ከኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ

**ሰኔ** 28 **ቀን** 2007 **ዓ/ም** (July 5, 2015 )

የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ በተከታታይ በሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ግንባር (ወያኔ) መራሹና በሰሜን ሱዳን መንግሥት መካከል በምስጢር የሚደረገውን የድንበር ውል እየተከታተለ ሲያጋልጥ የነበረና ዛሬም ጉዳዩን በቅርበት እየተከታተለ ደባውን ይፋ እያደረገ ይገኛል።

በድንበሩ ዙሪያ የሚደረጉ የድብቅ ውይይቶችንና የሚደረስባቸውን ስምምነቶች በሁለቱ አገሮች ሕዝቦች መካከል በሰላም አብሮ በጉርብትና መኖርን የሚያሳጣና ክልሉን የጦርነት ቀጠና ሊያደርገው እንደሚችል ባለፉት በርካታ ዓመታት በጽሑፍና በመገናኛ ብዙኀን ለጉዳዩ ባለቤት ለሆነው ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ በተደጋጋሚ አስገንዝበናል።

ይኸን የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት የተጻረረ ድርድርና በተደረሰበት ስምምነት መሠረት የተሰጠውን የድንበር መሬት በተመለከተ ከኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ በተጨማሪ በአገር ቤትና በውጪ የሚገኙ የማኅበረሰብና የፖለቲካ ድርጅቶች፤ ታዋቂ ግለሰቦችና ምሑራን እንደመሰከሩት፤ ሱዳንን የሚያዋስነው ረጅሙ የኢትዮጵያ ድንበር በጀግኖች ወገኖቻችን የሕይወትና የደም ዋጋ የተከፈለበት፣ በአካባቢው የሚገኘው ሕዝብና በተከታታይ መንግሥታት ተከብሮና ተጠብቆ ለትውልድ ያወረሱት የብሔራዊና የግዛት አንድነታችን መገለጫ፤ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የማንነታችን ነፀብራቅ ነው። ዜጎች ለሕይወታቸው የሚመኩበት ለልማትና ለአገር ደህንነት ቁልፍ የሆነ፣ ማእድን፣ ለም መሬት፣ ወንዝ፣ ተራራ፣ የዱር እንስሳት፣ ደንና በርካታ የተፈጥሮ ሀብት የሚገኝበት ነው። በመሆኑም ይህን የማንነታችን መግለጫ የሆነው ድንበር መሬታችን ለድርድር ሊቀርብ እንደማይገባና ሊቀርብም እንደማይችል አስገንዝበናል፤ ዛሬም በጥብቅ ለማሳወቅ እንወዳለን።

የሱዳን ትሪቢዩን ጋዜጣ (Sudan Tribune) በJune 21, 2015 (**ሰኔ** 14 **ቀን** 2007 **ዓ/ም** ) እንደዘገበውና የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥንና ሬዲዮ (ኢሳት) በሥርጭቱ እንደገለፀው ዛሬ የወያኔ አገዛዝ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሁኖ የሚያገለግለው የቀድሞው የአማራ ክልል የበላይ ባለሥልጣንና ከሱዳን መንግሥት ጋር የድንበር ውሉን ተደራድሮ የፈረመው አቶ ደመቀ መኰንን አዲስ አበባ ከተማ በተካሄደ መንግሥታዊ ስብሰባ ላይ ከተገኙ ተሳታፊዎች ለቀረበለት ጥያቄ ሲመልስ "የኢትዮጵያ መንግሥት የአገሪቱን ለም መሬት አሳልፎ ለሱዳን መንግሥት አልሰጠም" ብሏል። ይህን አባባል፤ በአንድ አፍ ሁለት ምላስ እንዲሉ ቀደም ሲል የተፈራረመውን ውልና ያደረገውን የአገር ክህደት ረስቶ ዛሬ ለምን እንደሚክድና እንደሚያስተባብል ሊገባን አልቻለም።

በድጋሚ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲያውቀው፣ በተለይም አዲሱ ትውልድ እንዲገነዘበውና ወደፊትም በዚህ ጉዳይ ላይ ለሚነሱ ክርክሮች እንደ ማስረጃ እንዲቀርብ የምንፈልጋቸውን ዋና ዋና ማስረጃዎችን እንደሚከተለው እናቀርባለን። ይኸውም፥

አንድ፡- እ.አ.አ በ1902 በአንድ በኩል የአፄ ምኒልክ መንግሥት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ግብፅንና ሱዳንን በበላይነት ይመራ ከነበረው ከቅኝ ገዥው የእንግሊዝ መንግሥት ጋር የተዋዋሉት ውል ግልጽ መሆኑን በተደጋጋሚ በጥናት በተደገፈ ማስረጃ አቅርበናል። ይህንን ውል መሠረት በማድረግ ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊና ለአፍሪቃ አንድነት ማኅበር ዋና ኃላፊ ወያኔ ከዚህ ውል ውጭ የሚያደርገውን ማንኛውንም ስምምነት እንደማንቀበል አቋማችን አስመዝግበናል። አሁንም በተደጋጋሚ ልናሰምርበት የምንፈልገው ዓበይት ጉዳይ፤ ወያኔ የፖለቲካ ሥልጣን ከመያዙ በፊት የነበሩት የአፄ ምኒልክ፣ የአፄ ኃይለ ሥላሴና የደርግ መንግሥታት የሚሉት ተመሳሳይ መሆኑን ነው። ይኼውም የውሉ አንቀጽ አንድ አስኳል የሆኑ የድንበሩ አመልካቾችን ያሳያል። የውሉ አንቀጽ ሁለት ድንበሩን ለመቸከል ሁለቱ መንግሥታት ተወካዮቻቸውን ሰይመው የተወከሉት ሰዎች በተገኙበት ብቻ የድንበሩ አቸካከል ድርድርና ተግባራዊነት ይፈፀማል፤ ለሕዝብም ይፋ ይሆናል የሚል ነው። ይህም የሚደረገው አፄ ምኒልክ በፈረሙትና በቀይ ምልክት ባደረጉበት ካርታ መሠረት ብቻ ነው። ተከታታይ መንግሥታት ይህን ውል እንደተቀበሉና የኢትዮጵያን ድንበር መብት እንዳስከበሩ ካሉት በርካታ መረጃዎች በተጨማሪ በሕይወት የሚገኙት የቀድሞው የኢትዮጵያ መሪ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማሪያም ስለ ጉዳዩ ኢሳት ባቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ አረጋግጠዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ሳያውቀውና ሳይስማማበት በሌላ መንግሥት ወይንም ተወካይ የተደረገ ውል ተቀባይነት እንደሌለውም አስምረውበታል።

ሁለት፡- የአፄ ምኒልክ መንግሥት ሳያውቀውና ሳይስማማበት፤ የእንግሊዝ መንግሥት በራሱ ውሳኔ ሻለቃ ቻርለስ ግዌን የተባለ መኃንዲስ ሠይሞ በፈለገውና በመሰለው መንገድ የሱዳንና የኢትዮጵያን ድንበር አድኋዊ በሆነና ኢትዮጵያን በጎዳ መንገድ የቸከለው የድንበር ምልክት በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ተቀባይነት አግኝቶ አያውቅም። ስለሆነም፤ የወያኔ አገዛዝ ራሱ በፈጠረውና ትርጉም በሰጠው ወይንም ወዳጁና ባለውለታው የሆነውን የሱዳን መንግሥት ለመጥቀም የኢትዮጵያን መብት የሚጻረረ ድርድርና አዲስ የድንበር ምልክት ችከላ ተቀባይነት የለውም። ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኰንን "የኢትዮጵያ መንግሥት የቀድሞውን ውል አፀደቀ እንጅ መሬት አልሰጠም" ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ግልፅ የማድረግ ኃላፊነት አለበት እንላለን። "ውሉን አስፈጸመ" ሲል ምን ማለቱ ነው? ተከታታይ መንግሥታት የተመሩበትን አፀደቀና አስከበረ ወይንስ ኢትዮጵያን የሚጎዳ ውል ተፈራርሞ ሥራ ላይ አዋለ? ይህን መመለስ ያለበት የወያኔ አገዛዝ ነው። የኢትዮጵያን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ያደረጋቸው ጥናቶችና ሌሎች እውቅና ያላቸው የታሪክና የሕግ ባለሞያዎች ያረጋገጡት የወያኔ አገዛዝ መቀበልና ማክበር ያለበት። ግዌን ኃላፊነት በጎደለው የኢትዮጵያ መንግሥትና ተወካዮች በሌሉበት፤ የውሉን አንቀፅ ሁለት በተፃረረና ባፈረሰ ሁኔታ እ.አ.አ በ1903 የቸከለው የድንበር መለያ ችካል ተቀባይነት እንደሌለው ነው። በተጨማሪም ግዌን ችካሉን ሲቸክል የግል ውሣኔ አድርጎ ወደ ኢትዮጵያ ሃያና ስድሳ ኪሎ ሜትር ገብቶ ብዙ የኢትዮጵያ መሬት ለሱዳን እንዲሰጥ አድርጓል። ይህ እንግሊዞችንና ሱዳንን ወክሎ ያደረገው ግፍ የውሉን አንቀጽ አንድና አንቀጽ ሁለት ሙሉ በሙሉ ይጻረራል። በራሱ ግንዛቤ ያደረገው አቸካከል በግሉ በራሱ ውሣኔ እንደሆነ ተቀብሏል (Gwen noted that he acted "ultra-virus," meaning, he went beyond his power. ይህም ማለት- ግዌን እራሱ እንደዘገበው ከተሰጠው ሥልጣን በላይ መሄዱን አምኗል።) ከወያኔ አገዛዝ በስተቀር ተከታታይ የኢትዮጵያ መንግሥታትና እኛ የምንለው ግዌንና የወከለው የእንግሊዝ መንግሥት የኢትዮጵያ መንግሥት ሳይፈቅድ፤ ሳይፈርምና ተወካዮች ሳይልክ ግዌን

ይኼን ለማድረግ በፍጹም መብት የለውም፤ አይችልም። ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅምና ግዛታዊ አንድነት አንፃር ሲታይ ደግሞ በጭራሽ ተቀባይነት የሌለው ነው።

ሶስት፦ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኰንን የወያኔ አገዛዝንና የአማራውን ክልል በመወከል 1,600 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለውን መሬት "ለሱዳን ሰጥቷል" የሚለውን ትችትና አቤቱታ አስተባብሏል። እኛ የምንጠይቀው ከላይ በአንድና በሁለት ያቀረብነው የኢትዮጵያ ተከታታይ መንግሥታት መመሪያ የሆነው መርህ ተጥሷል ወይንስ ተከብሯል የሚል መሠረታዊ የፖሊሲ ጥያቄ ነው። "የኢትዮጵያ መንግሥት አንድም ኢንች መሬት አልሰጠም"፤ የአማራው ክልል ኃላፊዎች የድንበር ድርድር ለማድረግ መብት የላቸውም" ብሏል።

አራት፦ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ የተናገረው የወያኔ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ከሰጠው መግለጫ ጋር ተመሳሳይነት አለው። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያለው "እኛ የተከተልነው ከእኛ በፊት የነበሩ መንግሥታት የተቀበሉትን ውል ከሥራ ላይ ማዋል ብቻ ነው" የሚል ነው። ሁለቱም ባለሥልጣናት የሚናገሩት ከእውነቱ የራቀ የመንግሥት ክህደት ብቻ ሳይሆን ተከታታይ መንግሥታት ያልተቀበሉትንና ከሥራ ላይ ያላዋሉትን የግዌንን ጎጂ የድንበር ችከላ ለሱዳን መንግሥት ጠበቃ በመሆን ስኬታማ ለማድረግ የሚደረግ ጥረትና የክህደቶች ሁሉ ክህደት መሆኑ ነው። ከላይ በቁጥር አንድ ላይ እንዳቀረብነው ግዌን የቸከለውን ድንበር ተከታታይ የኢትዮጵያ መንግሥታት እንዳልተቀበሉት በሕይወት የሚገኙት የቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬዚደንት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም በምሥክርነት ቀርበው በኢሳት አማካይነት ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለታሪክ ሠፌ መግለጫ ሰጥተውበታል። እኛም ደጋግመን ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያምንና ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀን የምንጠይቀው ያለፉት መንግሥታት ከሱዳን መንግሥት ጋር የፈረሙት የተለየ ውልና የችከላ ድርድር ካለ ለኢትዮጵያ ሕዝብ በአስቸኳይ ማስረጃውን እንዲያቀርቡ ነው። ነገር ግን የአገርን ጥቅም አሳልፎ ለመስጠት የሚደረግ ሤራ በህዝብ፣ በታሪክና በሕግ የሚያስጠይቅ እንደሚሆን አንጠራጠርም።

አምስት፦ በተከታታይ በማስረጃ እንዳቀረብነውና ወደፊትም እንደምናቀርበው የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት፣ ብሄራዊ አንድነትና ደኅንነት፣ የረጅም ጊዜ እድገትና ጥቅም፣ የሕዝቦቿን ሕይወትና የኑሮ መሻሻል፣ የአገሪቱን ሰላም አደጋ በሚጥል ሁኔታ ከሱዳን ሕዝብ ጋር ያላትን ታሪካዊና ተሳስቦና ተከባብሮ የመኖር ግንኙነት… ወዘተ ለወዳጁ ለሱዳን መንግሥት መካካሻ ለማድረግ ምንም ሥልጣንና መብት የለውም። ይህን ክህደት የኢትዮጵያ ህዝብ ሊታገለውና ሊያጋልጠው እንደተነሣ እምነታችን ነው።

ስድስት፦ ሌላው የወያኔ ባለሥልጣናትና ሥርዓታቸው ለኢትዮጵያ ሕዝብ እየደጋገሙ የሚናገሩት ውሸት በቅርቡ አቶ ደመቀም ይፋ ያደረገው ጉዳይ ነው። ይኼውም፤ እ. አ. አ. በ1996 በኢትዮጵያ ከፍተኛ አለመረጋጋት የተከሰተበትን ሁኔታ በመጠቀም ሱዳን ወይንም የሱዳን ዜጎች የኢትዮጵያን ድንበር ተሻግረው የወሰዱትን ለም መሬት የኢትዮጵያ መሆኑ እያወቁ ገጽ 3

ወያኔ ከሱዳን ነጥቆ ወስዶት የነበረውን ነው የመልስነው ያለውን ነው። ይህ የተገላቢጦሽ አባባል የወያኔ መሪዎች የሱዳን መንግሥት የዋለላቸውን ውለታ ለመክፈል የሚደረግ ሤራ መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው። የሱዳን ትሪቡን ጋዜጣ እንዳስነበበው "However, the Ethiopian government says it only gave back lands occupied in 1996 which belongs to Sudanese farmers adding no single individual from both sides was displaced at the borders as a result." (የኢትዮጵያ መንግሥት የሚለው ግን፤ እ.አ.አ. በ1996 የያዝኩትን የሱዳን ገበሬዎች ይዞታዎች የነበሩትን መሬቶች ነው መልሸ የሰጠሁት፤ እንዲሁም በዚሁ ሳቢያ በሁለቱ ወገኖች በኩል በድንበሩ ላይ ያለ አንድም ግለሰብ የተፈናቀለ የለም።) በወቅቱ የወያኔ መከላከያ ሚኒስትር የነበረውና በጉዳዩ ላይ የቅርብ እውቀት ያለው አቶ ስየ አብርሃ "ኢትዮጵያ ከሱዳን መሬት አልወሰደችም። እንዲያውም ሱዳን የወቅቱን አለመረጋጋት በመጠቀም የኢትዮጵያን መሬት ወስዳ

ስለነበር ያንን መሬት ነው ያስመለስነው" በማለት በወቅቱ የወያኔ ባለሥልጣናት የተናገሩትን ውድቅ በማድረግ የጻፈው ጽሑፍ በተለያዩ ድረ-ገጾች ቀርቧል።

በመጨረሻም፦ የኢትዮጵያና የዓለም ሕዝብ እንዲያውቀው የምንፈልገው ጉዳይ የወያኔ አገዛዝ ጫካ ውስጥ በሚታገልበት ወቅት የመሣሪያ፣ የገንዘብ፣ የስለላ ተባባሪ፣ አጋርና አመቻች፣ መግቢያና መውጫ ሆኖ በግልፅና በማያሻማ ሁኔታ ያገለገው አገርና መንግሥት ሱዳን ነው። ወያኔ 39ኛውን በዓል በየካቲት 11, 2006 ዓ/ም በመቀሌ ሲያከብር በበዓሉ የተገኘው የሱዳኑ ጄኔራል አል ፋታህ የተናገረው ዋቢ ነው። “እኔም፣ ሌሎችም አብረን ተባብረን ወያኔን ለድል አብቅተነዋል። እኔም ወያኔ ነበርኩ፤ አሁንም ነኝ…….መለስና አል ባሽር የሚተማመኑ ወንድማማቾች በአል በሺር ቤተ መንግሥት እየተገናኙ የተመካከሩ፤ የኢትዮጵያን መንግሥት በጋራ የተዋጉ፤ ማስረጃ የተለዋወጡ፤ የወያኔን ተልእኮ የተጋሩ ነበሩ… ወያኔ ድል እንደተጎናፀፈ መሪዎችን በሱዳን ልዩ አውሮፕላን ከካርቱም ወደ አዲስ አበባ አጅበው ከሄዱት መካከል ነበርኩበት…” ወዘተ ሲል በአል በሺር መንግሥትና በወያኔ መካከል ያለውን የጠነከረ ግንኙነት አስምሮበታል። ስለሆነም፤ የህወሓት መሥራቾችና መሪዎች የሱዳን ባለውለታ መሆናቸው ምንም አያከራክርም። እኛ የምንከራከረው፤ ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔ ውለታ ከፋይ መሆን የለባቸውም ነው።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ የህወሓት አገዛዝ “አንድም ኢንች መሬት ለሱዳን አልሰጠም፤ የሚያስፈፅመው ተከታታይ መንግሥታት የተዋዋሉትን ብቻ ነው። ለሱዳን የሰጠነው መሬት ኢትዮጵያ የወሰደችውን ነው” የሚለው ሁሉ የውሸት ክምር ከመሆን ያለፈ ፋይዳ የለውም። "ውሸት ቢደጋገም እውነት አይወጣውም"። የኢትዮጵያ የድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ማንኛውም በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖረውን አገር ወዳድ ሁሉ የሚጠይቀውና የሚያሳስበው ወያኔ የሚያካሂደውን ኢትዮጵያን የሚጎዳ ሕገ ወጥ የድንበር ውል አፈጻጸም መቃወም ታሪካዊ ግዴታው መሆኑን ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብና የኢትዮጵያ የመከላከያ ኃይል የአገሪቱን ዳር ድንበር፤ ግዛታዊ አንድነትና ሉዓላዊነት የማስከበር ኃላፊነት አለበት። የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያን መሬት ለማንም የውጭ አገር የማስተላለፍ መብት እንደሌለውና ነገ ጠዋት ደግሞ በኢትዮጵያ ሕዝብና በታሪክ ተጠያቂ የሚያደርገው መሆኑን በድጋሚ አስረግጠን እናሳውቃለን።

የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በቆራጥ ልጆቿ ይከበራል!

ድል ለጀግናው የኢትዮጵያ ሕዝብ!

ኢትዮጵያ በክብር ለዘለዓለም ትኑር!

**ኢትዮሚድያ - Ethiomedia.com**
**July 5, 2015**